

ለ 2022-23 የትምህርት ዘመን

# መመዝገብ

# እንኳን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በደህና መጡ

## የወላጆች መመሪያ መጽሃፍ

Arlington, Virginia    www.apsva.us

Arlington Public Schools

# ማውጫ

**የበላይ ተቆጣጣሪው እንኳን ደህና መጡ ..... 2**
**የእርስዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትአማራጮች ..... 3**
**የትምህርት ቤት መረጃ ክፍለ ጊዜያት እና የዝውውር ሂደት ለ 2022-23 ትምህርት ዘመን ..... 3**
**APS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ..... 4**
ዋክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 4
ዋሽንግተን-ሊብሪቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 4
ዮርክታውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 5
H-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም ..... 5
የአርሊንግተን ኮሚኒቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 5
አርሊንግተን የሙያ ማዕከል ..... 6
አርሊንግተን ቴክ ..... 6
የላንግስተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጣይ ..... 6
ኒው ዳይሬክሽን ..... 7
ኤኒስ ኬኔዲ ሺቨር ፕሮግራም ..... 7
ቶማስ ጄፈርሰን ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ፌርፋክስ) ..... 7
**ተማሪዎን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማስመዝገብ ..... 8**
የወቅቱ የአርሊንግተን ተማሪዎች ..... 8
የኮርሶች ምርጫ/የአካዳሚክ እቅድ ማውጣት ..... 8
አዲስ ተማሪዎች ..... 8
የእርስዎን ልጅ ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ..... 8
የጤና መስፈርቶች ..... 8
አስፈላጊ ክትባቶች ..... 8
የሚመከሩ ክትባቶች ..... 8
የስፖርቶች ተሳትፎ ..... 9
**ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች ጠቃሚ ምክር ..... 9**
**ማውጫ ..... 9**
**APS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በታዎችና ወሰኖች ካርታ ..... የጀርባ ሽፋን**

አርሊንግተን ዘርን፣ ብሄራዊ አመጣጥን፣ የሃይማኖት መገለጫን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ጾታን፣ እድሜን፣ የኢኮኖሚ ሁኔታን፣ የጾታ ዝንባሌን፣ እርግዝናን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ የዘር መረጃን፣የጾታ ምንነትን ወይም አገላለጽን፣ እና/ወይም የአካል ጉዳትን መሰረት ያደረገ መድልዎን ይከለክላል። ይህ ፖሊሲ ለኮርሶችን እና ፕሮግራሞች፣ ለምክር አገልግሎቶች፣ ለአካል ብቃት ትምህርት እና አትሌቲክስ፣ ለሙያ ትምህርት፣ ለመምህራን እና ከስርዐተ ትምህርት ውጪ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች እኩል ተደራሽ አድርጎ ያቀርባል። የዚህ ፖሊሲ ጥሰት ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ዋና ሃላፊ በ 703 228-6008 ወይም ለሰብዐዊ መርጃዎች ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ በ 703-228-6110 ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

Arlington Public Schools

ሕዳር 2021

**ውድ ቤተሰቦች፣**

እንኳን ደስ አላችሁ! የእርስዎ ልጅ በቅርቡ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሄዱበትን እና ስለወደፊቱ እድሎቻቸው የሚያስቡበትን ጉዞ ይጀምራሉ።

አርሊንግተን ውስጥ፣ ከሌሎች በርካታ አካዳሚክ አማራጮች ጋር አሳታፊ የሆነ የማስተማሪያ እና በማህበራዊ ደረጃ ደጋፊ የሆነ አካባቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስላሉን ደስተኞች ነን።የአጠቃላይ የልጅን ፍላጎት ማሟላት ማለት ለተማሪዎች አካዳሚክስ እና ማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነት ቅርጠን እንሰራለን፤ ለተማሪ ስኬት ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ ክበቦችን፣ ስነ ጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ስፖርቶች እና ከስርዐተ ትምህርቱ ውጪ የሆኑ ተግባራትን እናቀርባለን፣ እንዲሁም ተማሪዎች ደህንነት እና ድጋፍ እንዲሰማቸው የሚያግዙ የታመኑ አዋቂዎች እንዳሉን እናረጋግጣለን ማለት ነው።

ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግር ተማሪዎች እና ተሰቦች የተማሪዎችን የወደፊት እቅዶች እንዲያመቻቹ እና እንደገና ትኩረት እንዲሰጡ መልካም አጋጣሚ ይሰጣል። ይህ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተለውጦ ሊሆን ስለሚችል ከተማሪዎች ጋር ስለ ትምህርት ግቦቻቸው እና የስራ ፍላጎቶቻቸው ለመወያየት ይህ አመቺ ጊዜ ነው። ተማሪዎች ስለ ራሳቸው ብዙ የተማሩ ሲሆን በወረርሽኙ ወቅት ብዙ ልምድ ነበራቸው፤ አዲስ ፍላጎቶችን አግኝተው ወይም ደግሞ በሚወዷቸው ርዕሶች ላይ ፍላጎት አጥተው ሊሆን ይችላል፣ ይህም ለመጪው የሁለተኝ ደረጃ ሽግግር ለማቀድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ማግኘት የቻሉ ሲሆን ለአንዳንድ አርስቶችም ፍላጎቶችን አላሳደሩም ለመጪው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግር ለማቀድ እንደ ሁኔታ የሚጠቀም ይሆናል። ሽግግሩን ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች እንከን የለሽ እንዲሆን ለማድረግ በዚህ አለን።

በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የማማከር እና የስራ ትምህርት ሰራተኞች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወቅት እና ከዚያ በኃላ ቤተሰብዎ አማራጮችን በሚፈልግበት ጊዜ ድጋፍ እና መመሪያ ይሰጣሉ። በተጨማሪም የእርስዎን ተማሪ ፍላጎቶቻቸውን የሚያንጸባርቁ እና ለምርቃት የሚስፈልጉ ኮርሶች እና ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግቦችን ጨምሮ የአራት አመት አካዳሚ እቅድ እንዲያሳድግ እርዳታ ይሰጣሉ። የአካዳሚ እቅዱ ግልባጭ እርስዎን እንዲገመግሙት  እና ግብዓት እንዲያደርጉት ወደ ቤት የሚላክ ይሆናል። ለተማሪዎች ስኬት እና ደህንነት ምን አይነት ድጋፎች እንዳሉ በመነጋገር የእርስዎ ተማሪ ስለገለጻቸው ሃሳቦች እና ፍላጎቶች ከትምርህት ቤቱ ርእሰ መምህር፣ አማካሪ እና አስተማሪዎች ጋር ይጋሩ። እቅዱ ተማሪዎ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ከምረቃ በኃላ በሚኖረው ሕይወት ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

እንደ ሂሳብ፣ ሳይንስና የውጪ ቋንቋዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው አስቀድመው በሚወሰዱ በአካዳሚክስ አስቸጋሪ የሆኑ ኮርሶች ላይ ከተማሪዎ ጋር እንዲወያዩ አበረታታዎታለሁ። እነዚህ ኮርሶች የእርስዎን ተማሪ በተሻለ ስለ ድህረ ሁለተኛ ደረጃ እና የስራ እድሎች ማወቅ እንዲችል እና እንዲዘጋጅባቸው እገዛ መስጠት ይጀምራሉ። ሁሉም ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህታቸው ወቅት አንድ ወይም ከዘ በላይ የሆነ ከፍተኛ ምደባ/AP/ ወይም ባለሁለት የምዝገባ ትምህርቶችን እንዲወስዱ አበረታታለሁ—ይህም ተማሪዎች ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ሕይወት ችግሮች እንዲዘጋጁ ያግዛል። ይህ የኮርስ ስራ በተጨማሪም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ ቢሆንም የኮሌጅ ክሬዲት ማግኘት ያስችላሉ።

በ [www.apsva.us/engage](www.apsva.us/engage) በኦንላይን ከሚገኘው የ2018-2024 ስትራቴጂክ እቅድ ጋር ራስዎን እንዲያላምዱ አበረታታዎታለሁ። ስትራቴጂክ እቅዱን ሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ጤናማ፣ ፍትሃዊ እና ደጋፊ የትምህርት አካባቢዎች እንዲማሩ እንዲያድጉ ያደርጋል እንዲሁም ሁሉንም ተማሪዎች ወደ ስኬት እንዲሄዱ የሚያበረታታ የተካተተ ማህበረሰብን ያቀርባል::::

በ [www.apsva.us](www.apsva.us) ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎቻችን በኩል የAPSን ወቅታዊ ዜናዎች ያግኙ። በወቅቱ ስላለው የማህበረሰብ የተሳትፎ እድሎች መረጃ ያግኙ እና በAPS ድረገጽ *"ከAPS ጋር ይሳተፉ"*በሚለው ክፍል ውስጥ አስተያየት ይስጡ። የማህረሰብ ግብዓት እና የተቀናጀ ትብብር የሂደቱ ወሳኝ ከአካል ሲሆን APS ማደጉን እና የተማሪዎቻችንን የወደፊት ህይወት በአውንታዊ መልኩ የሚቀርቀርጹ ውሳኔዎችን መስጠቱን ቀጥሏል። በዚህ አጋርነት ውስጥ እንደ APS ልጅዎ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያለው ልምድ የበለጸገ እና ስኬታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከእርስዎ ጋር አብረን መስራት እንፈልጋለን።

ከሰላምታ ጋር፣

ፍራንሲስኮ ዱራን Ed.D.
ዋና ተቆጣጣሪ

## የእርስዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትአማራጮች

ሁሉም ተማሪዎች በተለየ የትምህርት ላይ መገኘት/የወሰን ዞን ወደተዘጋጀውየአካባቢ ትምህርት ቤቶች እንዲመዘገቡ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። (የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ለመወሰን በጀርባ ሽፋኑ ላይ ያለውን ካርታ ይመልከቱ፣ በ703-228-8000 ላይ ይደውሉ ወይም ወደ APS ድረገጽ፣ apsva.us/boundaries ይሂዱ)። ተማሪዎች ለአማራጭ ትምህርት ቤት/ፕሮግራም ወይም ወደ የአጎራባች ትምህርት ቤት ሽግግርን ወደ ሚቀበል **ትምህርት ቤት የበላይ ተቆጣጣሪ አመታዊ የትምህርት ቦርድ ማሻሻያ ላይ በመመስረት** ማመልከት ይችላሉ።

### አማራጭ ትምህርት ቤቶችና ፕሮግራሞች

በካውንቲው ውስጥ ያሉ ሁሉም ተማሪዎች በH-B Woodlawn ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም እና በአርሊንግተን የሙያ ማዕከል ውስጥ በአርሊንግተን ቴክ ላይ ለማመልከት ብቁ ናቸው።ማመልከት ይችላሉ። ኢንተርናሽናል ባካሎሪየት (IB) ፕሮግራም ዋሽግተን-ሊብረቲ እና ከፍተኛ ምደባ (AP) አውታር በዌክፊልድ አጎራባች ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ላሉ ተማሪዎች አማራጮች ናቸው።

**ለእነዚህ ፕሮግራሞች ለ2022-23 የትምህርት አመት አማ ራጭ የትምህርት ቤቶች ማመልከቻ ማቅረብ አለብዎት።**
በከፊል ስፓኒሽ መግቢያ ፕሮግራም ጉንስቶን ላይ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በኮርስ ምርጫ ሂደት በኩል ዌክፊልድ ስፓኒሽ መግቢያ ፕሮግራም ላይ መግባት ይችላሉ። **ለAPS እና/ወይም ለመግቢያ ፕሮግራሙ አዲስ የሆኑ ተማሪዎች በመግቢያ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ አማራጭ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።**

ቶማስ ጀፈርሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ (ፌርፋክስ) የመግቢያ መስፈርት ለሚያሟሉ ተማሪዎች ክፍት ነው፤ የትምህርት ቤቱን ማመልከቻ ማቅረብ አለብዎት (ገጽ 7 ይመልከቱ)።

የትምህርት ቤት ባስ ትራንስፖርት በማንኛውም ከላይ በተዘረዘሩ ፕሮግራምች ለተመዘገቡ ብቁ ተማሪዎች ይቀርባል።

ለ2022-23 የትምህርት አመት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጭ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ703-228-8000 ላይ ይደውሉ ወይም የ APS ድረገጽ *apsve.us/school-optinos* "አማራጮችና ዝውውሮች" ወደሚለው ክፍል ይሂዱ።

### ወደ አጎራባች ትምህርት ቤቶች ዝውውሮች

**በትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲ J-5.3.31 መሰረት፣ አጎራባች ትምህርት ቤቶች የገንዘብ እጥረቶችን እና የአቅም ገደቦችን በተሰታቸው መጠን ዝውውሮችን ይቀበላሉ።** ለ2022-23 የትምህርት አመት ዝውውሮችን ስለሚቀበሉ ስለ አጎራባች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ70-03-800 ላይ ይደውሉ ወይም ወደ APS ድረገጽ፣ *apsva.us/school-options* "አማራጮች እና ዝውውሮች" የሚለው ክፍል ላይ ይሂዱ።

## የትምህርት ቤት መረጃ ክፍለ ጊዜያት እና የዝውውር ሂደት ለ2022-23 ትምህርት ዘመን

### አማራጭ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

ለ2022-23 ትምህርት ዘመን ለአማራጭ ትምህርት ወይም ፕሮግራም ማመልከቻ የጊዜ ገደብ ከሕዳር 1/2021 እስከ ጥር 21/2022 ነው።

የአማራጭ ትምህርት ቤቶች እና የፕሮግራሞች ማመልከቻ በኢንተርኔት በጥር 21/2022 እስከ 4 ፒ.ኤም. መቅረብ አለበት። በኢንተርኔት ማመልከቻውን መሙላት እገዛ ለማግኘት፣ እባክዎ ወደ እንኳን ደና መጡ ማዕከልን በ703-228-8000 ላይ ይደውሉ፣ ወይም ወደ APS ድረገጽ *apsve.us/school-optinos* "አማራጮች እና ዝውውሮች" የሚለው ክፍል ላይ ይሂዱ።

### ወደ አጎራባች ትምህርት ቤቶች ዝውውሮች

በ2022-23 ትምህርት አመት ወደ አጎራባች ትምህርት ቤት ዝውውር ማመልከቻ ጊዜ ከየካቲት 21/2022 እስከ መጋቢት 11/2022 ነው።

ወደ አጎራባች ዝውውር ትምህርት ቤት ማመልከቻ በትምህርት ቤት እስከ መጋቢት 21/2022 እስከ 4 ፒ.ኤም ድረስ መሞላት አለበት። በኢንተርኔት ማመልከቻውን ለመሙላት እገዛ ለማግኘት፣ እባክዎ ወደ እንኳን ደና መጡ ማዕከል በ703-228-8000ይደውሉ፣ ወይም ወደ APS ድረገጽ *apsva.us/school-options* "አማራጮች እና ዝውውሮች" የሚለው ክፍል ላይ ይሂዱ።

### ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረጉ የመረጃ ክፍለጊዜዎች

ወላጆች በአጎራባች ትምህርት ቤቶታቸው እና/ወይም በአማራጭ የትምህርት ቤት/ፕሮግራም የመረጃ ክፍለጊዜዎች ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። የትምህርት ቤት የመረጃ ክፍለጊዜ ቤተሰቦች ስለትምህርት ቤቱ የበለጠ እንዲያውቁ፣ የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች እንዲያገናኙ፣ እና ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤትምንነት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያስችላል።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ቨርችዋል የመረጃ ክፍለጊዜዎችን ያስተናግዳሉ። ሁሉም ክፍለጊዜዎች ይመዘገባሉ እናም ከአካል ግንኙነት ክፍለጊዜ በኃላ በኢንተርኔት ይቀርባሉ። የመረጃ ክፍለጊዜዎች ማስፈንጠሪያዎች በ *apsva.us/school-options/high-school-choices/high-school-information-sessions/* ላይ ይገኛል።

| INFORMATION SESSIONS | |
|---|---|
| አርሊንግተን ቴክ<br>703-228-5800 | ክፍለ ጊዜ 1: ሕዳር 10, 2021 7:00 ፒ.ኤም.<br>ክፍለ ጊዜ 2: ታሕሳስ 7, 2021 7:00 ፒ.ኤም. |
| H-B ዉድልዋን<br>703-228-6363 | ጥር 10, 2022 7:00 ፒ.ኤም. |
| ዎክፊልድ<br>703-228-6700 | AP ኔትዎርክ: ሕዳር 9, 2021 7:00 ፒ.ኤም.<br>መግቢያ: ሕዳር 9, 2021 7:45 ፒ.ኤም. |
| ዋሽንግተን ሊብራቲ<br>703-228-6200 | ታሕሳስ 1, 2021 7:00 ፒ.ኤም. |
| ዮርክታውን<br>703-228-5400 | ታሕሳስ 8, 2021 7:00 ፒ.ኤም. |

## ዋክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*የAP ካፕስቶን ትምህርት ቤት*
*የአመቱ ዓለም አቀፍ የስፓኒሽ አካዳሚ ትምህርት ቤት*
*የኮሌጅ ቦርድ ተመስጦ ሽልማት ትምህርት ቤት*
*ጥብቅነት፣ ግንኙነቶች፣ ተቋቋሚነት፣ ኃላፊነት፣ ውጤቶች*

**ዶክተር ክሪስ ዊልሞር፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-6700 · 703-575-8832 (ፋክስ)
1325 South Dinwiddie Street, Arlington, Virginia 22206
wakefield.apsva.us

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



ዌክፊልድ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ወላጆች ለስኬት አብረው የሚሰሩ ንቁ ማህበረሰብ ነው፡ ፡ እጅግ በጣም ዘመናዊ በሆነ ሕንፃ ውስጥ፣ ዌክፊልድ ለሁሉም ተማሪዎች ተገቢውን የትምህርት ፈተናዎችን ይሰጣል። ዘጠና ሁለት በመቶው ተመራቂዎች ወደ ኮሌጅ ይቀጥላሉ፣ እና በ2021 ተመራቂዎች በስኮላርሺፕ እና በስጦታ ገንዘብ 12 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ አግኝተዋል።

ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች በማፍራት የዌክፊልድ ተነሳሽነቶች ትምህርት ቤቱን ሁለት ጊዜ በጎበኙት ፕሬዝዳንት ኦባማ ትኩረት እንዲያገኝ አድርገው ነበር። በተጨማሪም፣ የበፊቱ የቨርጂኒያ ገዢ ቴሪ መክ ኦሊፌ በዋና ፕሮጀክታችን በመደሰቱ በ2016 ዌክፊልድ ላይ አዲስ የዲፕሎማ እቅዱን አሳውቋል።

ዌክፊልድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስፓኒሽ መግቢያ ፕሮግራም ቤት ሲሆን፣ እንደ ኢንተርናሽናል ስፓኒሽ አካዳሚ እንዲሆን በስፔን የትምህርት ሚኒስቴር ተወክሏል። በእያንዳንዱ አመት የስፓኒሽ ኤምባሲ ሁሉንም የመግቢያ ፕሮግራም ላጠናቀቁት ከአምባሳደሩ የምስክር ወረቀት በመስጠት እውቅና ይሰጣል። እንዲሁም ፈረንሳይኛ፣ ላቲን፣ ጀርመንኛ፣ ማንዳሪን፣ ጃፓንኛ፣ እና አረብኛን ያቀርባል።

የእኛ ከፍተኛ ምደባ (AP) አውታር ተማሪዎች የከፍተኛ የምደባ ኮርሶች እንዲወስዱ በማበረታት ያዘጋጅል።

ዌክፊልድ ለዚህ ተነሳሽነት በኮሌጅ ቦርድ ከፍተኛ የምስጋና ሽልማት በክብር ያገኘ ሲሆን በከፍተኛ የትምህርት አመታቸው ላይ ለተማሪዎች ከፍተኛ ካፕስቶን ዲፕሎማን፣ ገለልተኛ የምርምር ፕሮጀክትን፣ በተለይም የሙያ ፍላጎት ዘርፍን ያቀርባል።

የዘጠነኛ ክፍል ፋውንዴሽን ለአካዳሚክ ልህቀት፣ የዌክፊልድ የሽግግር ፊርማ አቀራረብ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ከዋና ቡድን ዘርፍ አስተማሪዎች ጋር ያደራጃል። ይህ የዘጠነኛ ክፍል አቀራረብ ለተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው የመጀመሪያ አመት ከፍተኛ ድጋፍ ያቀርባል

የኮሆርት እና የተባበሩት የአናሳ ሴቶች ፕሮግራሞች አናሳ ተማሪዎች የአካዳሚክ ትምህርቶችን እንዲወስዱ እና ወደ ኮሌጅ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲሸጋገሩ ለመደገፍ ይሰራሉ። ኮሆርት ፕሮግራም ከአፍሪካን-አሜሪካን እና ሂስፓኒክ ወንዶች ጋር የሚሰራ ሲሆን፣ የተባበሩት የአናሳ ሴቶች ለሁሉም አናሳ ሴቶች ክፍት ነው።

ከጠንካራ ማህበራሰባዊ ግንኙነቶች ጋር፣ ዌክፊልድ በትምህርት ውስጥ በካርታ አጋሮች አሉት። አንዱ ተማሪዎች በፕሮፌሽናል የመድረክ ስራዎች እንዲሳተፉ የሚያስችል ቲያትር ነው። ዌክፊልድ በተጨማሪ የተመረጡ የበላይ አካሎች ጋር በዘርፉ በክፍያ የስራ ላይ ልምድ እንዲያገኙ ከከተማ ህብረት ጋር በአጋርነት ይሰራል።

## ዋሽግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*የIB አለም አቀፍ ትምህርት ቤት*
*የትምህርት ቦርድ የክብር ስኬት ሽልማት፣ 2017፣ 2018*

**አንቶኒዮ ሆል፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-6200 · 703-524-9814 (ፋክስ)
1301 North Stafford Street, Arlington, Virginia 22201
wl.apsva.us

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



ዋሽግተን-ሊበርቲ በአርሊንግተን ውስጥ ከተመሰረቱት ሶስት አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ ነው፡ ፡ ስራም ከጀመረ በአሁኑ ወቅት በ96ኛ አመቱ፣ትምህርት ቤቱ ከ100 በላይ ክበቦች እና ድርጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ ከመላው አለም ከ70 በላይ ሀገራት የመጡ የተለያዩ የተማሪዎችን ስብጥር የያዘ ነው። ዋሽግተን-ሊበርቲ በታሪኩ እና ባህሎቹ የሚኮራ ሲሆን፣ ይህም በአሜሪካ የትምህርት ክፍል፣ በቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ፣ በቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል፣ እና በዋሽግተን ፖስት የተሰጥኡ ክብርን ያካትታል። ዋሽግተን-ሊበርቲ በቨርጂኒያ የትምህርት ቤት ቦርዶች ማህበር እንደ "የስኬት ማሳያ" ቀርቧል።

ዋሽግተን-ሊበርቲ ውስጥ ዘጠነኛ ክፍል የሚገቡ ተማሪዎች በ9ኛ ክፍል ግንኙነቶች፣ ከመካከለኛ ትምህርት ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግባት ሂደትን ለማቅለል በሚያስችል የሽግግር ፕሮግራም ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በአነስተኛ የትምህርት ማህበረሰቦች በአራት ዋና የትምህርት አይነት ዘርፎች አስተማሪዎች እና የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች፣ እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) አስተማሪ ለእንግሊዘኛ ተማሪዎች በቡድን ተደራጅተዋል።

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከአስተማሪዎች፣አስተዳዳሪዎች፣ እና አማካሪዎች የተቀናጀ ድጋፍ ያገኛሉ።

ኢንተርናሽናል ባኪሊውሌሬተር (IB) ዲፕሎማ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው በዋሽግተን-ሊበርቲ በ1998 የመጀመሪያ 13 ተማሪዎች ተመርቀዋል ሲመረቁ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ 1,231 ተማሪዎች ከቨርጂኒያ ከፍተኛ ጥናቶች ዲፕሎማ ጋር በመተባበር በIB ዲፕሎማ ፕሮግራም ውስጥ ተሳትፈዋል። በርካታ ሌሎች ተማሪዎች የግል IB የምስክር ወረቀት ኮርሶችን ወስደዋል። ስኬታማ የB ኮርሶችን እና ፈተናዎችን ማጠናቀቅ የኮሌጅ ክሬዲትን እና/ወይም በኮሌጅ እና በዩኒቨርስቲዎች ከፍተኛ ደረጃንማግኘት ያስችላል።

ዋሽግተን-ሊበርቲ በተጨማሪም ተማሪዎችን ወደ ኮሌጅ ክሬዲት ሊመራ የሚችል የመውጫ ፈተና የሚጠይቁ የከፍተኛ ምደባ (AP) ኮርሶችን ይሰጣል። ተማሪዎች የAP ክፍሎችን የመጀመሪያ አመት ተማሪ እያሉ መጀመር ይችላሉ።

ዋሽግተን-ሊበርቲ የ2021 ምሩቆች በነጻ የትምህርት እድል ከ20 ሚሊየን ዶላር በላይ ሽልማቶችን አግኝተዋል። ዘጠና ሁለት በመቶ የሚሆኑት ምሩቆች፣ ከ81 በመቶ በላይ በሆነ የ4 አመት ኮሌጆች እና የዩኒቨርስቲዎች ምዝገባ፣ በቀጥታ ወደ

የዋሽንግተን-ሊበሪቲ የአረጋውያን ልምድ ፕሮግራም፣ *ስራን ከጽንሰ ሃሳብ ወደ ተግባር ማሰስ*፣ አሁን 17ኛ ዓመቱን ይዟል። በ2021 የአረጋውያን ልምድ ፕሮግራም ላይ ዘጠና ስምንት በመቶ የሚሆኑ አረጋውያን ተሳትፈዋል።

## ዮርክ ታውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*ብሔራዊ የልህቀት ትምህርት ቤት*
*የኤድ ቦርድ: የተከበረ የስኬት ሽልማት 2014-17፣2021*

**ዶክተር ኬቨን ክላርክ፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-5400 · 703-228-5409 (ፋክስ)
5200 Yorktown Boulevard, Arlington, Virginia 22207
yhs.apsva.us

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*




በዮርክ ታውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ፍትሃዊነትን፣ ፣ልህቀትን፣ እና መነቃቀትን ማሳካት ችለናል። ይህ ቁርጠኝት በዮርክ ታውን፣ ዮርክ ታውን ROCS - ሌሎችን፣ ማህበረሰብዎን፣ እና ከምንም በላይ ራስዎን ያክብሩ በመባል በሚታወቀው ልዩ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት(SEL) ላይ ተንጸባርቋል! ዮርክ ታውን ለዚህ ፕሮግራም በባህሪ ትምህርት አጋርነት እና በክላውዲያ ዶድሰን የስፖርት፣ የስነ ምግባር እና የታማኝነት ሽልማትን እንደ "ብሄራዊ የባህሪ ትምህርት ቤት" እውቅና ተሰጥቶታል።

ዋሽግተን ፖስት በሜትሮ አካባቢ ካሉት በአካዳሚክ ፈታኝ ከሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ዮርክታውን አንዱ ነው እናም ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ የዮርክታውን ተመራቂዎች የድህረ ሁለተኛ ትምህርትን ይቀጥላሉ። የዮርክታውን ተማሪዎች በበርካታ የስነ ምግባር ኮርስ ስራዎች እንዲሁም በከፍተኛ ምደባ (AP)፣ በባለሁለት ምዝገባ (DE)፣ እና በሙያ እና ቴክኒካል ትምህርት (CTE) ኮርሶች ይሳተፋሉ።

ዮርክታውን የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት በሰፊ የስርዓተ ትምህርት እና በበርካታ ፕሮግራሞች እና የድጋፍ ኔትዎርኮች እንደ አርበኞች ክፍለ ጊዜ ማማከር፣ ዘጠነኛ ክፍል ውስጥ በቡድን የሚማሩት በርካታ የስነ ምግባር የአለም ታሪክ፣ የአቻ ተማሪዎች ቁጥጥር፣ እና አጠቃላይ የአትሌቲክስ እና የእንቅስቃሴ ፕሮግራምን ያቀርባል። ተጨማሪ የተማሪ ድጋፎች የጽሁፍ ድጋፍ ማዕከልን፣ የሂሳብ ልቦራቶሪን፣ እና የታለሙ የድህረ ትምህርት አካዳሚክ እርዳታን ያካትታሉ። ጨምሮ የሂሳብ ላብ፣የአርበኞች ክፍል ድጋፎች እና ከትምህርት ቤት በኃላ ኢላማ የተደረገ የአካዳሚክ እገዛ ያካትታል።

የዮርክታውን "የፍትሃዊነት፣ የአመራር እና የህዝብ አገልግሎት ማዕከል" በርካታ የተማሪ ፕሮግራሞችን በአመራር፣ በአገልግሎት፣ በፍትሃዊነት እና በማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት ውስጥ ያዘጋጃል።በተጨማሪም ዮርክታውን በመላው የትምህርት ቤት ፕሮግራም ለማህበረሰብ ግንባታ በጎ የተማሪ እና ሰራተኛ ግንኙነት የመመለስ ተግባራትን ይፈጽማል።

ኒወርክ ታዎን የአጠቃላይ-ልጅ ትኩረት ከፍተኛው ልምድ ሲሆን ለእነዚህ ለገሀዱ ሕይወት እና ልምድ ማግኘት የስራ መስመር እንዲፈጽም እድል ይሰጣል።

ለሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊነት እና ተደራሽነት ላይ ትኩረት በመስጠት ለልህቀት በርካታ
መንገዶች በማመቻቸት ተማሪዎችን ለማበልጸግ ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት ላይ ዮርክታውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመማር እና ለማደግ እጅግ የላቀ ቦታ ነው።

## H-B ውድላዋን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም

*የሃገር አቀፍ ፕሮግራም*

ዶክተር ኬሲ ሮቢንሰን፣ ርዕሰ መምህር
703-228-6363 · 703-558-0317 (ፋክስ)
1601 Wilson Boulevard, Arlington, Virginia 22201
hbwoodlawn.apsva.us



H-B-ውድላዋን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም በአራት ምሰሶዎች የቆመ ነው እነዚህም፡ ተንከባካቢ ማህበረሰብ፣ የግል አመራር፣ ፍትሃዊነት፣ እና ራስ መር መማር ናቸው። እያንዳንዱ ተማሪ፣ አስተማሪ እና ወላጅ እኩል ድምጽ በሚያገኝበት፣በተማሪዎች መር ኮንፈረንሶች፣ ተመራጮች እና ክበቦች፣ እና በሳምንታዊ የከተማ ስብሰባዎች በኩል፣ ማህበሰረቡ ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ግቦቻቸውን እንዲያሳድጉ እና እንዲያሳኩ እንዲሁም የቤተሰብነት ስሜት እንዲሰማቸው በጋራ ይሰራል።

የተማሪዎች ምርጫ ለH-B ውድላዋን አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም ማዕከላዊ ትኩረት ነው። ተማሪዎች ግዴቶቻቸውን ለመወጣት ጊዜቸውን በማስተዋል እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መወሰን አለባቸው። የግል-መር ጊዜ መጠን በሂደት ከክፍል 6 ወደ 12 ከፍ ይላል። ይህንን የነጻነት ስራ አቅርቦት ለመስራት፣ ትምህርት ቤቱ የተማሪዎቹን ጥሩ ፍላጎቶች በመተማመን ስለ ግል ሀላፊነት እሴት ያስተምራል። በ1971፣ "ለአስተዋይ አንድ ቃል በቂ ነው" የሚለው አባባል ነጻነትን ከሃላፊነት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማንጸባረቅ እንደ ትምህርት ቤቱ መሪ ቃል ተመርጦ ነበር። እያንዳንዱ ተማሪ በተለያዩ ራስን የመቻል እና የግል መነሳሳት ደረጃዎች በH-B ውድላዋን ውስጥ ይገባል። ፋክሉቲው ከተማሪዎች ጋር እንደ ግለሰቦች፣ በአነስተኛ ቡድኖች እና በትምህርት ደረጃ በመስራት በትምህርት ፕሮግራምቻቸው ላይ ከፍ ያለ ቁጥጥር ኢንዲያገኙ ያስችላል። H-B ወድላዋን በተጨማሪም የግለሰብ ተማሪዎችን ፍላጎቶች በእኛ የአስተማሪ ማማከር ፕሮግራም በኩል ተደራሽ በማድረግ፤ እያንዳንዱ ተማሪ በህንጻው ላይ ከአዋቂ ጋር ግንኙነት እንዳለው እናጥ ሁሉም ቤተሰቦች ተገቢ የሆነ ግንኙነት ነጥብ እንዳላቸው ያረጋግጣል። አስተማሪዎች እና TAዎች እያንዳንዱ ተማሪ የአካዳሚክ እና የማህበራዊ ችሎታቸው ላይ እንዲደርሱ ለማረጋገጥ ከቤተሰቦች ጋር በጋራ ይሰራሉ።

የእኛ ተልዕኮ የH-B ውድላዋን ምሩቃን ትአባላቶቹን በሚያበረታታ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ላለ ህይወት በብስለት፣ ወደ እውነታው እንዲቀርቡ በሚያዘጋጃቸው ማህበረሰብ ውስጥ የመሆን እና የመማር ልምድን ለH-B ውድላዋን ተመራቂዎች ማቅረብ መቻል ነው።

## አርሊንግትን ኮሚኒቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*የካውንቲ አቀፍ አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት*
***ዶክተር ባርባራ ቶምፕሰን፣ ርዕሰ መምህር***
703-228-5350 · 703-521-0139 (ፋክስ)
800 S. Walter Reed Drive, Arlington, VA 22204
achs.apsva.us

የአርሊንግተን ማህበረሰብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜያቸው 16 ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የካውንቲ ነዋሪዎች በሴሚስተር (በአንድ ሴሚስተር የተጠናቀቁ ትምህርቶች) ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ የሚያስፈልጉ ኮርሶችን ለቀን ትምህርቶች፣ እና ለአመት (በአመት የተጠናቀቁ ትምህርቶች) ለከሰአት በኋላ ትምህርቶችን የሚያቀርብ አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።] ትምህርቶቹ የሚሰጡት ከ 8 ኤ.ኤም. -



9፡10 ፒ.ኤም ሰአት ነው። እንደ ካውንቲ አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምዝገባ፣ አርሊንግተን የማህበረሰብ ሁለተኛ ትምህርት ቤት የራሱን ዲፕሎማ ይሰጣል። ACHS የ2021 የቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ ተከታታይ የማሻሻያ ሽልማት አግኝቶ ነበር። የአርሊንግተን ኮሚኒቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለያዩ ተማሪዎች ለኮሌጅ፣ ለስራ፣ እና ለወደፊት ራሳቸውን እያዘጋጁ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ማግኘትን ያተኮሩ ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መስፈርቶችን በሚያጠናቅቁበት ወቅት፣ ተማሪዎች ለባለ ሁለት ምዝገባ ኮሌጅ ክሬዲት ትምህርቶችን የመውሰድ፣ እንዲሁም ከNOVA አማካሪዎች ጋር በመስራት የኮሌጅ ሽግግርን እንከን የለሽ በሆነ መልኩ የማቀድ እድል አላቸው። ከአርሊንግተን የሙያ ማእከል ቀጥሎ ያለው ቦታ የሙያ እና የቴክኒክ ኮርሶችን ለማጠናቀቅ፣ የኢንዱስትሪ ሰርተፊኬቶችን ለማግኘት፣ እና ተጨማሪ የኮሌጅ ድርብ ምዝገባ ክሬዲቶችን ለማግኘት ተጨማሪ እድሎችን ይሰጣል።

የአርሊንግተን ማህበረሰብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚከተሉትን ይሰጣል፡-

- የተማሪዎችን የመርሃግብር ፍላጎቶች እና የኮርስ መስፈርቶችን ለማሟላት የጊዜ መርሐግብር ውስጥ ተለዋዋጭነት፤
- በአንድ ዓመት ውስጥ ስምንት ወይም ከዚያ በላይ ክሬዲቶችን የማግኘት እድል፣ ክሬዲትን ለማፋጠን ወይም ክሬዲትን መልሶ ለማግኘት፤
- ተማሪዎች በግላቸው የመማር ችሎታን እንዲያሳዩ የሚያስችላቸው በብቃት ላይ የተመሰረቱ ትምህርቶች፤
- ምርጫ - ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ ለመሄድ ይመርጣሉ፤
- በ 16 አመት ወይም ከዚያ በላይ የመግባት እድል፤ ከፍተኛ የዕድሜ ገደብ የለም (ከትምህርት እድሜ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የትምህርት ክፍያ አለ)፤
- የኮሌጅ ክሬዲት ለአንዳንድ የNOVA ኮርሶች የኮሌጅ ክሬዲት በድርብ ምዝገባ ፕሮግራም በኩል፤ እና
- ግላዊ ትምህርት፣ ብዙ ጊዜ በትናንሽ ትምህርቶች የተማሪዎችን የመማሪያ ዘይቤ፣ ወይም በመስመር ላይ ቅርጸት ለማሟላት። አስተማሪዎች እና ሰራተኞች ደጋፊ እና ግላዊ ሁኔታን አዳብረዋል።

በአርሊንግተን ማህበረሰብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ማነጋገር አለባቸው፣ ወይም ለምዝገባ መረጃ እና ሪፈራል አሁን ያላቸውን የትምህርት ቤት አማካሪ ማግኘት አለባቸው። ለመረጃ፣ ለክሬዲት ግምገማ፣ ለፕሮግራም ማቀድ፣ እና/ወይም ለምዝገባ ቀጠሮ ለመያዝ ለትምህርት ቤቱ ይደውሉ።

## አርሊንግተን የሙያ ማዕከል

*የአስተዳዳሪ የሙያ እና የቴክኒክ አካዳሚ*

**ማርጋሬት ቹንግ፣** *ርዕሰ መምህር*
703-228-5800 · 703-228-5815 (ፋክስ)
816 Walter Reed Drive, Arlington, Virginia 22204
careercenter.apsva.us

### አርሊንግተን ቴክ በሙያ ማእከል

አርሊንግተን ቴክ ጠንካራ፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ ተማሪዎች በኮሌጅ እና በስራ ቦታ በትብብር ችግር ፈቺ እንዲሆኑ የሚያዘጋጅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ነው። ተማሪዎች በእውነታው ዓለም ችግሮችን ለመፍታት እና ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሙያ እና ቴክኒካል ትምህርት (CTE) ክፍሎች የሚያዳብሩትን የስነምግባር ዋና አካዴሚያዊ እውቀታቸውን በብቃት እንዴት ማዋሃድ እንደሚችሉ ይማራሉ።



አርሊንግተን ቴክ ተማሪዎች በሰሜን ቨርጂኒያ ማህበረሰብ ኮሌጅ (NVCC) ድርብ ምዝገባ በማድረግ የቅድሚያ ኮሌጅ ክሬዲቶችን በማግኘት በተለያዩ የ CTE ፕሮግራሞች እንዲያስሱ እና የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ እና ኮሌጅ ለመጀመር ዕድሉን ይሰጣል። ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች የአጠቃላይ ትምህርት ሰርተፍኬት እና/ወይም ተባባሪዎች ዲግሪ ማግኘት ይችላሉ። እንደ የፕሮጀክት-ተኮር የመማር ልምድ ማጠቃለያ፣ የአርሊንግተን ቴክ ተማሪዎች እንደ ተለማማጅ፣ አማካሪ፣ ወይም እንደ ገለልተኛ ተመራማሪዎች ለመስራት የሚቀጠሩበትን የአንድ አመት ከፍተኛ የካፒታል ፕሮጀክት ያጠናቅቃሉ። በአርሊንግተን ቴክ መማር ንቁ (በመጠየቅ)፣ ትክክለኛ (በፕሮጀክቶች)፣ እና በተማሪዎቹ ፍላጎት የተነሳ ነው።

የሙያ ማዕከሉ ተልዕኮ በ25 ልዩ የሙያ እና ቴክኒካል ትምህርት (CTE) ፕሮግራሞች በIT እና በዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ በሙያ ማመልከቻ፤ በኢንጂነሪንግ እና በኢንዱስትሪ ንግዶች፤ በጤና እና በህክምና አገልግሎቶች፤ እና በህዝብ እና በሰብዐዊ አገልግሎቶች በኩል "በመስራት የመማር ፍላጎትን ማፍራት" ነው። በነዚህ የሙያ እና የኮሌጅ ዝግጁነት ፕሮግራሞች፣ የሙያ ማዕከል በገበያ ቦታ ክህሎቶች፣ በኢንዱስትሪ ማረጋገጫዎች፣ በኮሌጅ ክሬዲቶች እና ስራን መሰረት ባደረጉ እድሎች በኩል የተሻሻሉ እድሎችን ያቀርባሉ። ተማሪዎች ለእነዚህ የCTE ትምህርቶቻቸው በየቀኑ ከቤታቸው ወደ ትምህርት ቤት የስራ ማዕከል ይመጣሉ።

ከሰሜን ቨርጂኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ (NVCC) ጋር በመተባበር ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን እና የኮሌጅ ክሬዲቶችን በCTE እና በአካዳሚክ ኮርሶች በኩል ምዝገባ ማግኘት ይችላሉ።

በሙያ ማዕከሉ ውስጥ ተጨማሪ ፕሮግራሞች አካዳሚውን፣ የእንግሊዘኛ ተማሪ ተቋምን፣ የስራ ቅጥር ዝግጁነት ፕሮግራምን፣ እና የታዳጊ ወላጅነት ፕሮግራምን ያካትታል።

CTEን እና የአካዳሚክ ትምህርቶችን በሙያ ማዕከሉ ውስጥ መውሰድ የሚፈለጉ ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን አማካሪ ማግኘት አለባቸው።

## የላንግስተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጣይ ፕሮግራም

***ዶክተር ፊሊፕ "ቺፕ" ቦናር፣ አስተዳዳሪ***
703-228-5295 · 703-807-0614 (ፋክስ)
2121 North Culpeper Street, Arlington, Virginia 22207
hsc.apsva.us



ላንግስተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጣይነት ፕሮግራም ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ የሚያገኙበትን አማራጭ መንገድ ይሰጣል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በአጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ተማሪዎች ለተመሳሳይ ኮርስ መስፈርቶች፣ ለክሬቶች ብዛት፣ እና ለSOL ምዘና ማረጋገጫ ሀላፊነት ቢኖርባቸውም፣ ፕሮግራሙ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ እና የጊዜ ሰሌዳ ተለዋዋጭነት ያቀርባል። ላንግስቶን ውስጥ፡

- ተማሪዎች በአመት ስምንት ወይም ከዛ በላይ ክሬዲቶች ማግኘት ይችላሉ።

- ትምህርቶች ሴሚስተርን መሰረት ያደርጉ ናቸው፣ እናም ተማሪዎች ክሬዲት ለማግኘት ወይም ለማፋጠን በሴሚስተር አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት ወይም አራት ክፍሎች ሊያጠናቅቁ ይችላሉ።
- የተማሪው የገንዘብ ወጪ በእድሜ ይለያያል።
- ተማሪዎች ላንግስተን ለመማር ይመርጣሉ ወይም በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሊመሩ ይችላሉ።
- ተማሪዎች ላንግስተን ውስጥ ለመግባት ቢያንስ 16 አመት የሆነናቸው መሆን አለበት፤ ከዚያ በላይ የእድሜ ገደብ የለውም።
- መስፍርቶች እንደተሟሉ፣ ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው መደበኛ ወይም ከፍተኛ ጥናት የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ይቀበላሉ።
- የኮሌጅ ክሬዲት ለአንዳንድ ኮርሶች ከሰሜን ቨርጂኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ (NVCC) በባለሁለት ፕሮግራም ምዝገባ በኩል ይገኛል።

በዲዛይን አነስተኛ በሆነ ፕሮግራም ውስጥ በመሰራቱ፣ አስተማሪዎች እና ሰራተኞች ደጋፊ እና የግል አካባቢን ፈጥረዋል። አስተማሪዎች በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን እና በበርካታ ደረጃዎች ወይም የትምህርት አይነቶች የሚማሩ ተማሪዎችን በማስተማር ክህሎት ያላቸው ናቸው።

## ኒው ዳይሬክሽንስ

***ዶክተር ፊሊፕ "ቺፕ" ቦናር፣ አስተዳዳሪ***

703-228-2117 · 703-875-8290 (ፋክስ)

2121 North Culpeper Street, Arlington, Virginia 22207

newdirections.aspva.us

የኒው ዳይሬክሽን ፕሮግራም በአነስተኛ እና በሚያሳድግ አካባቢ ውስጥ የሚታወቁ ተማሪዎች በጥብቅ የአካዳሚክ መርሃ ግብሮች እና በውጤታማ የምክር አገልግሎት ያቀርባል። በከፍተኛ ደረጃ የተዋቀረ እና ደጋፊ የሆነ የአካዳሚክ ቦታ ተማሪዎች ለመመረቅ የሚያስፈልጋቸውን የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲቶች እንዲያገኙ እድል ይሰጣቸዋል። ከዚህ በታች ተዘረዘሩት ባህሪያት በኒው ዳይሬክሽን ውስጥ አሁን በተመዘቡ ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

- ተማሪው እድሜው ቢያንስ 14 አመት ሲሆን በትምህርቱ ቢያንስ ዘጠነኛ ክፍል ላይ ደርሷል።
- ተማሪው በፍርድ ቤት ቁጥጥር ስር ነው እና የሙከራ ሃላፊ አለው።
- ተማሪው በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ችግር አጋጥሞታል።
- ተማሪው ጥብቅ ክትትል የሚደረግበት የትምህርት ቤት አካባቢ ያስፈልገዋል።
- ተማሪው በቤት ትምህርት ቤቱ/ቷ ድጋፍ ያገኘ/ች ሲሆን በአጣሪ ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝቷል/አግኝታለች።

ኒው ዳይሬክሽን ሶስት ዋና ግቦች አሉት፡ የአካዳሚክ ደረጃን ማሻሻል፣ በጎ ባህሪን መገንባት እና የሙከራ ጊዜ ግዴታዎች በስኬት ማጠናቀቅ ናቸው። ተማሪዎች በአካዳሚክ ግቦች ላይ እድገት ማሳየት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ቤተሰቦች የትምህርት ቤት ስራን በቤት ውስጥ ለማጠናቀቅ ፕሮግራሞችን ለማበልጸግ ከሰራተኞች ጋር እንዲያገናኙ ያበረታታሉ።

ተማሪዎች ከበርካታ መንገዶች በአንዱ የኒው ዳይሬክሽን ፕሮግራም ያጠናቅቃል፡ (ሀ) የAPS የምርቃ መስፍርቶች ማሟላት እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቅ፤ ለ) ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታቸው ቤት መመለስ ፤ወይም ሐ) ላንግስተን ውስጥ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ቀጣይ ፕሮግራም መዘዋወር ናቸው።

## ኢውኒስ ኬኔዲ ሼሪቨር ፕሮግራም ልዩ ትምህርት፣ ከክፍል 6-12

**ጆርጅ ሄዋን፣ ርዕሰ *መምህር***

703-228-6440 · 703-247-3162 (ፋክስ)

1601 Wilson Boulevard, Arlington, Virginia 22201

shriver.apsva.us

ሼሪቨር ፕሮግራም በአዕምሯዊ ችግሮች ምንያት ሰፊ ፕሮግራም ትግበራዎች ለሚያስፈልጋቸው እድሜአቸው 11-22 ለሆኑ ተማሪዎች ልዩ ትምህርት ይሰጣል። ከዚህም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ክፍል እና የማህበረሰብ መርጃዎች ይጠቀማል። እንደ አርሊንግተን የቀጣይ አገልግሎቶች ቁርጠኝነት አካል፣ ፕሮግራሙ ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ከአዋቂ ጋር እንዲሆኑ ለማገዝ መመሪያን ይሰጣል። የወላጆች እና የማህበረሰቡ ኤጀንሲዎች የእቅድ ማውጣት እና የአገልግሎቶች ዋና አካል ናቸው። የሼሪቨር ፕሮግራም ተማሪዎች ማህብረሰቡ ውስጥ ይሰራሉ እናም በስራ ጣቢያዎች ላይ በተደጋጋሚ ሽግግሮችን ያደርጋሉ። የሽግግር እቅዶች የሚጀምሩት በ14 አመት እድሜ ቢሆንም፣ ትክክለኛው የጉዳይ አስተዳደርር ከአዋቂ አገልግሎቶች ጋር የሚጀምረው ከ18 አመት በፊት ነው።

የአዋቂ ማህብረሰብ ዝግጅት የሼሪቨር ፕሮግራም ዋንኛ ግቡ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት፣ በርካታ ፕግራሞች የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት ለማሟላት ተዘጋጅተዋል። የመመሪያ ዘርፎችየሙያ እና ማህበሰረብ ክህሎቶችን፣ የቀን ኑሮ ክህሎቶችን፣ የትርፍ ጊዜን፣ ግንኙነትን፣ መዝናኛን፣ እና ሌሎች ገለልተኛ ክህሎቶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው።

## የቶማስ ጀፈርሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ (ፌርፋክስ)

6560 Braddock Road, Alexandria, VA 22312

tjhsst.fcps.edu

**ጄረሚ ሹገርት፣ *የምዝገባ ዳይሬክተር***

TJHSST የምዝገባ ቢሮ

8115 Gatehouse Road, Falls Church, VA 22042

571-423-3770 · 571-423-3777 (ፋክስ)

ኢሜል፡ tjadmissions@fcps.edu

www.TJAdmissions.org

ቶማስ ጀፈርሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ (TJHSST) የፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ አካዳሚክ-አመት የአስተዳዳሪው ትምህርት ቤት ሲሆን፣ አጠቃላይ የኮሌጅ የመሰናዶ ፕሮግራም በዋናነት በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢንጅነሪንግ እና በሂሳብ ላይ ያተኩራል። ማንኛውም በ8ኛ ክፍል የተመዘገበ እና ቀጣይ አልጀብራ 1(ወይም ከፍተኛ ደረጃ የሂሳብ ኮርስ) የተመዘገበ የAPS ተማሪ ማመልከት ይችላል። ተማሪው ቅበላ ካገኘ፣ ሁሉም የትምህርት ክፍያዎች በAPS ይከፈላሉ እናም ትራንስፖርት ይሰጣል።

**ማመልከቻዎች ጥቅምት 25 ተከፍተው ሕዳር 19 ይዘጋሉ።** ተማሪዎች ቅዳሜ ጥር 29፣ የጹሁፍ ፈተና የሚወሰዱ ሲሆን ፈተናው አርሊንግተን ካውንቲ ትምህርት ቤት በአካል እንደሚወሰድ ይገለጻል። ስለ ትምህርት ቤቱ የበለጠ መረጃ እና ስለምዝገባሂደቱ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት www.TJAdmissions.org ን ይጎብኙ። ጥያቄ ካለዎት ለምዝገባ ጽ/ቤቱ በ571-423-3770 ላይ ይደውሉ ወይም በ mailto:tjadmissions@fcps.edu ላይ ኢሜል ይጻፉ።

# ተማሪዎን ያስመዝግቡ

### የወቅቱ የአርሊንግተን ተማሪዎች

### የኮርሶች ምርጫ/የአካዳሚክ እቅድ ማውጣት

ከመካከለኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግርን ቀላል ለማድረግ የሁለተኛ ደረጃ አማካሪዎች በጥር መጨረሻ እና በየካቲት መጀመሪያ ላይ ከስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ለመገናኘት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይጎበኛል።ትምህርት ቤት መሰረት ያደረጉ የመረጃ ክፍለጊዜዎች ቤተሰቦችን አካዳሚክ አቅድ ማውጣት ላይ እንዲሰሩ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርስ ስራዎች ማወቅ እንዲችሉ ያግዛል።

በ *2022-23 - የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ጥናቶች*(POS) በመካለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥር ላይ የሚደረግ ሲሆን በAPS ድረገጽ *http://www.apsva.us* ላይ ይገኛል። POS የተዘጋጀው ወላጅ እና ተማሪ አጠቃላይ ፕሮግራምን እንዲያቅዱ እና የምረቃ መስፈርቶች እንዲሟሉ እና ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኃላ ለአማራጮች እንዲዘጋጁ ማስቻል ነው።

በቨርጂኒያ ምርቃት ስር አዲሱ የምርቃ መስፈርቶች በ2018 መጨረሻ (ክፍል 2023) ዘጠነኛ ክፍል በሚገቡ ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ለስታንዳርድ ዲፕሎማ እና አድቫንስድ ዲፕሎማ ስታንዳርድ ክሬዲቶች ተመሳሳይ ቢሆንም፣ ክሬዲቶችን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገው ብዛት-በበታው ያሉ ኮርሶች ማለፍ እና የኮርስ መጨረሻ ምዘና ለሁለቱም ዲፕሎማዎች ወደ አምስት ዝቅ ብሏል (በእንግሊዘኛ መጻፍ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ታሪክ/ማህበራዊ ሳይንስ)።

እያንዳንዱ የመካከኛ ትምህርት ቤት ተማሪ ከአራት እስከ ስድስት አመት አካዳሚክ እቅድ የሚኖረው ሲሆን ይህም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይከተላቸዋል። እቅዱ ከትምህርት ቤት አማካሪ ጋር ስብሰባ በሚደረግበት ወቅት በጸደይ ወራት በተማሪው ይሻሻላል። የኮርስ ጥያቄ ቅጽ (CRF) ከስብሰባው በኃላ የሚጠናቀቅ ሲሆን ይህም በተማሪ፣ በወላጅ እና በትምህርት ቤት አማካሪ መካከል በሚደረግ የትብብር ጥረት ነው። ስለ አካዳሚክ እቅድ ማውጣት ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የእናንተን ትምህርት ቤት የማማከር ድረገጽ ይብኙ ወይም የ APS ድረገጽ *apsva.us/academicplanning*ን ይጎብኙ።

## አዲስ ተማሪዎች

የእርስዎ ልጅ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ከእንግሊኛ ቋንቋ ሌላ ከሆነ፣ ወይም የትምህርት ስርዐትን ከሃገር ውጪ ሲከታተል ከነበረ፣ የቋንቋ አገልግሎት ምዝገባ ማዕከል (LSRC) በ703229-8000 በማነጋገር ልጅዎን ያስመዝግቡ። በሌሎች በሁሉም ጉዳዮች፣ ልጅዎን በአካባቢዎ ባለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም ልጅዎ ፈቃድ ያገኘበት ትምህርት ቤት ያስመዝግቡ።

### የእርስዎን ልጅ ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- የልጁ እድሜ እና ህጋዊ ስም ማረጋገጫ-የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ግልባጭ (የተረጋገጠው ግልባጭ መቅረብ ካልቻለ፣ የምስክርነት ቃል መሞላት አለበት። APS የዚህን የምስክርነት ቃል ግልባጭ ለህግ አስፈጻሚ ኮሚቴ የማቅረብ መብት አለው)።
- ወላጅ/ህጋዊ ሞግዚት አርሊንግተን ካውንቲ ነዋሪ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ - ወቅታዊ የኪራይ ውል ወይም የማስያዣ ስምምነት
- የሚመለከተው እና የሚገኝ ከሆነ፣ ከሌላ ትምህርት ቤት ወይም ካውንቲ ይፋዊ የትምህርት ቤት መዝገቦች
- ከመግባቱ በ12 ወራት ውስጥ የተደረገ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራን ክተባ መዝገቦች እና ሰነዶች ያካተተ የህክምና መረጃ (የጤና መስፈርቶችን ይመልከቱ)።

ለተጨማሪ መረጃ እና ለመመዝገቢያ ለሚያስፈልጉ ለሁሉም ቅጾች፣ ወደ ድረገጽ "የምዝገባ" ክፍል *www.apsva.us* ይሂዱ።

## የጤና መስፈርቶች

***ማሳሰቢያ፡ ተማሪ(ዎች) ከነዚህ ማሟያዎች ውጪ ትምህርት እንዲጀምሩ አይፈቀድላቸውም።***

**የአካል ምርመራ**

የተማሪው የህክምና መረጃ (ክትባት እና የአካል ምርመራ፣ ካለ) ለትምህርት ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል። ከትምህርት ቤት መግቢያ 12 ወራት በፊት የአካል ምርመራ ቢደረግ ይመከራል፣ ነገር ግን ተማሪው በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስፖርቶች የሚሳተፍ ካልሆነ አስፈላጊ አይደለም። የክትባት ሪከርድ ያስፈልጋል እናም የእያንዳንዱን ክትባት ወሩ፣ ቀን እና አመት መዘርዘር አለበት። ስለክትባቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከዚህ በታች ይመልከቱ።

## የሳንባ ነቀርሳ መስፍርቶች

ከትምህርት ቤት መግቢያ በ12 ወራት ውስጥ የተሰራ የሳንባ ነቀርሳ (TB) ማጣሪያ ሰነድ ያስፈልጋል። የቲቢ ማጣሪያ እና/ምርመራ አሜሪካ ውስጥ ወይም በአሜሪካ ተቋም መሰራት አለበት እናም ፈቃድ ባለው የህክምና ባለሙያ (ማለትም፣ ሀኪም፣ነርስ ሀኪም፣ የተመዘገበ ነርስ ወይም የሀኪም ረዳት) መረጋገጥ እና መፈረም አለበት። ማጣሪያው የበሽታ ምልክቶችን ግምገማ፣ የስጋት ምዘና፣ እና ከተለየ የቲቢ

የቆዳ ምርመራ ወይም ቲቢ የደም ምርመራ (በተለምዶ"IGRA" በመባል የሚታወቅ) ማካተት አለበት።ተብሎ የሚጠቀስ አስፈላጊ ነው።

## አስፈላጊ ክትባቶች

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ወቅታዊ የክትባት መዝገብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

**7ኛ ክፍል** የሚገቡ የሚያስፈልጋቸው፡

- ቲታነስ/ዲፍቴሪያ/ፐርቱሲ (Tdap)
- ማኒጅዎ ኮካል/ማጅራት ቆልፍ (MenACWY)
- HPV ክትባት(የመጀመሪያው መድሃኒት 7ኛ ክፍል ከመግባቱ በፊት ይሰጣል። ወላጆች ይህንን ክትባት ባለመውሰድ የHPV መስፈርትን "መዝለል" ይችላሉ።

**12ኛ ክፍል** የሚገቡ የሚያስፈልጋቸው፡

- ማንጅዎ ኮካል ማበረታቻ ክትባት

ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት ለዝቅተኛ የክትባት መስፍርቶች ዝርዝር፣ *vdh.virginia.gov/ immunization/requirements/* ን ይመልከቱ።

ስለ ጤና መግቢያ መስፈርቶች ወይም ክትባቶች ጥያቄዎች በህዝብ ጤና ነርስ ወይም በእያንዳንዱ የአርሊንግተን ትምህርት ቤት በትምህርት ቤት ጤና እገዛ ወይም በትምህርት ቤት ጤና ሃላፊ በ 703-228-1651 ሊመለሱ ይችላሉ።

## የስፖርቶች ተሳትፎ

ትምህርት ቤት ሲዘጋ ስፖርት ላይ ለመሳተፍ፣ ተማሪው በግንቦት 1 ወይም ከዛ በኃላ የተሞላ የአካል ምርመራ ቅጽ ሊኖረው ይገባል። ቅጾች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም [www.vhsl.org/forms/](www.vhsl.org/forms/) ላይ ማግኘት ይቻላል። የተሞሉ ቅጾች ወደ እርስዎ ልጅ ትምህርት ቤት የእንቅስቃሴዎች ዳይሬክተር መመለስ አለባቸው።

# ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች ጠቃሚ ምክር

የሚቀጥለው አመት ለእርስዎ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን አስደሳች እና አዲስ ልምዶች ያመጣለታል፣ ቀጣዮቹ አራት የትምህርት አመታት ደግሞ የአካዳሚክ እድገት፣ግኝት እና የተራዘመ ነጻነት ጊዜያት ይሆሉ። የእርስዎን ተማሪ ለመደገፍ አንዳንድ ጠቅሚ ምክሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- በትምህርት ቤቱ እና የእርስዎ ተማሪ ተግባራት ላይ **ይሳተፉ**።
- **የእርስዎ ተማሪ** የትምህርት ቤት ስራዎችን እና ሃላፊነቶችን ለመከታተል **ስርዐት እንዳለው** እና የቤት ስራዎችን እና ለመስራት መደበኛ መርሃግብር እንዳለው **እርግጠኛ ይሁኑ**።
- በእርስዎ ተማሪ ጥናቶች ላይ **ፍላጎት ያሳዩ**። በተደጋጋሚ ስለ የቤት ስራ እና ፕሮጀክቶች ይጠይቁ። ሁሉም መሰራቱን እና መረዳታቸውን ያረጋግጡ።
- በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ ክፍል የቀረበውን መረጃ ከተማሪዎ ጋር በመሆን **ያንብቡ እና ይገምግሙ**። ከእርስዎ ተማሪ ምን እንደሚጠበቅ ለማወቅ ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ምሽት ላይ ይሳተፉ።
- ከእርስዎ ተማሪ አማካሪ እና አስተማሪዎች ጋር **ግንኙነት ያድርጉ**።
- ተማሪዎ የእሱን/የእሷን አማካሪ እንዲያውቁ **ያበረታቱ**።
- **የእርስዎ ተማሪ** በመደበኛነት **ትምህርት ቤት መሄዱን ያረጋግጡ**።
- የእርስዎ ተማሪ አዲስ ፍላጎት እንዲኖረው አስፈላጊ ከሆነም በስፖርት፣ በክበብ፣ በጉዞ ፕሮግራምች ላይ እንዲሳተፍ **ያበረታቱ**።
- የእርስዎን ተማሪ **ጓደኞች ማንነት** እና እሱ/እሷ ሁልጊዜ የት እንደሚውል/እንደምትውል **ይወቁ**።
- ለተማሪዎ እገዛ ለማድረግ ወይም ለማዳመጥ፣ እና በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ **ከጎኑ እንደሚሆኑ በተደጋጋሚ ያስታውሱ**።
- ትምህርት ቤት ውስጥ **በወላጆች ስብሰባ በመሳተፍ** እንዴት ለትምህርት ቤት በጎ ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ይወቁ።
- ትምህርት ቤት ውስጥ የእርስዎን ተማሪ ጥረቶች **በቀጣይነት እውቅና በመስጠት ይሸልሙ**።

የሚከተሉትን ጨምሮ ብዙ አይነት መረጃዎችን ለማግኘት *PAPS ድረገጽ* ይጎብኙ፡ PK-12 መረጃዎች፣ የዲጂታል መሳሪያ እገዛ፣ የጥናቶች ፕሮግራም፣ የወላጅ አካዳሚ (ለወላጆች ነፃ ኮርሶች)፣ የ VDOE ስቴት ሪፖርት ካርዶች፣ እና ሌሎችም።

# ማውጫ

## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የአርሊንግተን ኮሚኒቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
ዶክተር ባርባራ ቶምፕሰን፣ ርዕሰ መምህር
800 S. Walter Reed Drive, 22204 · 703-228-5350
[achs.apsva.us](achs.apsva.us)

**ዋክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
ዶክተር ክሪስ ዊልሞር፣ ርዕሰ መምህር
1325 South Dinwiddie Street, 22206 · 703-228-6700
[wakefield.apsva.us](wakefield.apsva.us)

**ዋሽንግተን-ሊብሪቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
አንቶኒዮ ሆል፣ ርዕሰ መምህር
1301 North Stafford Street, 22201 · 703-228-6200
[wl.apsva.us](wl.apsva.us)

**ዮርክታውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
ዶክተር ኬቨን ክላርክ፣ ርዕሰ መምህር
5200 Yorktown Boulevard, 22207 · 703-228-5400
[yhs.apsva.us](yhs.apsva.us)

## ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች

**አርሊንግተን ቴክ/አርሊንግተን የሙያ ማእከል**
ማርጋሬት ቹንግ፣ ርዕሰ መምህር
816 South Walter Reed Drive, 22204 · 702-228-5800
[careercenter.apsva.us](careercenter.apsva.us)

**H-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም**
ዶክተር ኬሲ ሮቢንሰን፣ ርዕሰ መምህር
1601 Wilson Boulevard, 22201 · 703-228-6363
[hbwoodlawn.apsva.us](hbwoodlawn.apsva.us)

**የላንግስተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጣይ ፕሮግራም**
ዶክተር ፊሊፕ "ቺፕ" ቦናር፣ አስተዳዳሪ
2121 North Culpeper Street, 22207 · 703-228-5295
[hsc.apsva.us](hsc.apsva.us)

**ኒው ዳይሬክሽን**
ዶክተር ፊሊፕ "ቺፕ" ቦናር፣ አስተዳዳሪ
2121 North Culpeper Street, 22207 · 703-228-2117
[newdirections.apsva.us](newdirections.apsva.us)

**ኤኒስ ኬኔዲ ሺቨር ፕርግራም**
**(ልዩ ትምህርት፣ ዕድሜ 11-22)**
ጆርጅ ሄዋን፣ ርዕሰ መምህር
1601 Wilson Boulevard, 22201 · 703-228-6440
[shriver.apsva.us](shriver.apsva.us)

**ቶማስ ጄፈርሰን ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
ትምህርት ቤት፡ 6560 Braddock Road, Alexandria 22312
[tjhsst.fcps.edu](tjhsst.fcps.edu)
ጀረሚ ሹገርት፣ የምዝገባ ዳይሬክተር
የምዝገባ ቢሮ፡ 8115 Gatehouse Road, Falls Church, Virginia 22042 · 571-423-3770
[www.TJAdmissions.org](www.TJAdmissions.org)

# APS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦታዎችና ወሰኖች ካርታ




ማጣቀሻ

- ካውንቲ አቀፍ ሁለተኛደረጃ ትምህርት ቤት
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወሰኖች

Miles: 0 — 1 — 2 — 4

ማሳሰቢያ፡
የአካባቢዎን ትምህርት ቤት የእኛን የቦታ መፈለጊያ በመጠቀም ለመወሰን ከፈለጉ፣ ወደ APS (www.apsva.us) የ“ምዝገባ” ክፍል ይሂዱ።
ለበለጠ መረጃ፣ የትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን በ703-228-6005 ያግኙ።